# ላንድማርክ

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**1. ይህ ሂደት ፈጣን የሆነ የዕቅድ አወጣጥ ሂደት እንደሆነ ሰምቻለሁ። ይህ ምን ማለት ነው?**

የላንድማርክ ሞል ዳግም-እቅድ ሂደት 51-ኤከር ስፋት ላለው ሞል ብቻ በ2009 ላንድማርክ/ቫን ዶርን ኮሪደር እቅድ ላይ ማሻሻያ ማድረግ መቻልን ያካትታል። ምክንያቱም፤ የዚህ ሊደረግ የሚችል ማሻሻያ አድማስ የተገደበ ስለሚሆን እና በ2009 የሞል ቦታ እቅድ ላይ ብቻ መሰረት አድርጎ ስለሚሰራ ነው፤ የእቅድ አወጣጥ ሂደቱም እስከ ኤፕሪል 2019 ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

**2. በቀጣይ የሚደረጉ የማህበረሰብ ዝግጅቶችና የሚዳሰሱ ነጥቦች ምንድን ናቸው?**

በቀጣይ የሚደረጉ ዝግጅቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- የአማካሪ ቡድን/የማህበረሰብ ዎርክሾፕ - ጃንዋሪ 26፣ ከ 10 am እስከ 2 pm – ይህም ለአማካሪ ቡድን አባላት፣ ማህበረሰብ፣ ከተማ ሰራተኞች እና የንብረት ባለቤት ተወካዮች የእቅድ ማሻሻያውን በማዘጋጀት ረገድ ረቂቅ ምክረ ሃሳብ ለመንደፍ በጋራ እንዲሰሩ ለማስቻል በእጅጉ ጠቃሚ ዎርክሾፕ ነው። የመጓጓዣ አገልግሎት፣ የመሬት አጠቃቀም፣ ክፍት ቦታ እና የከተማ ዲዛይን ከሚነሱት ነጥቦች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው።
- የአማካሪ ቡድን/የማህበረሰብ ስብሰባ - ፌብሩዋሪ 27፣ ከ 7 እስከ 9 pm – ይህ ስብሰባ የፕረዘንቴሽን ይዘት ያለው ሲሆን የተወሰነው የስብሰባው ክፍል ከማህበረሰቡ አስተያየት ለማግኘት በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው። ከጃንዋሪ 26 ዎርክሾፕ ቀጥሎ፣ በእቅድ ኮሚሽንና የከተማ ምክር ቤት ኤፕሪል 2009 በሚያደርገው ስብሰባ ላይ የሚቀርቡ የ2009 አቅድ ማሻሻያዎችን አጠቃሎ ያቀርባል።

ስለማህበረሰብ ፕሮግራሙ ሁሉንም መረጃዎች alexandriava.gov/Landmark ከሚለው ድህረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል።

**3. የአማካሪ ቡድኑ አባላት በምን መልኩ ይመረጣሉ?**

በማርች 29 2016 ላይ የከተማው ምክር ቤት በ2717 ውሳኔ መሰረት ኤዲ ሆክ ኢስንሃወር ዌስት/ላንድማርክ ቫን ዶርን አስፈፃሚ አማካሪ ቡድን አዋቅሯል። የዚህ ቡድን ዓላማ በኢስንሃወር ዌስት ስሞል ኤሪያ እቅድና ላንድማርክ ቫን ዶርን ኮሪደር እቅድ መሰረት በመሰረተ ልማት እና የገንዘብ እቅዶች እና ተያያዥ የክትትል ጥናቶች ዙሪያ ለሰራተኞች መመሪያ መስጠት ነው። የአማካሪ ቡድኑ ማመልከቻ ከኤፕሪል 11 እሰከ ሜይ 2፣ 2016 ክፍት ሆኖ ቆይቷል። በውሳኔው ላይ እንደተጠቀሰው፣ ዘጠኙን አባላት በምርጫ ሂደት መሰረት የመረጣቸው የከተማው አስተዳደር ሲሆን፣ ለቀሩት አምስት ቦታዎች ደግሞ ቦርዶችና ኮሚሽኖች ተወካዮቻቸውን መርጠዋል።

አማካሪ ቡድኑ ለላንድማርክ ሞል ዳግም እቅድ ማውጣት ሂደት ወቅት በሙሉ እንደ የማህበረሰብ ማማከሪያ ፎረም ሆኖ ያገለግላል። የዌስት ኢንድ ንግዶችና የላንድ ማርክ ሞል ባለቤቶችን በተገቢ መልኩ መወከላቸውን ለማረጋገጥ፤ የከተማው ምክር ቤት ውሳኔ 2843 ን በጊዜያዊነት በማሻሻል አማካሪ ቡድኑ አንድ ቦታ ለዌስት ኢንድ ንግድ ማህበር፣ አንድ ጊዜያዊ ቦታ ለሀወርድ ሁጅስ ማህበር እንዲያካትት የወሰነ ሲሆን፣ ይህም ሂደቱ ሲጠናቀቅ የሚያበቃ ይሆናል። እነዚህ ተጨማሪ ቦታዎች በመጨመራቸው፣ ከሁለቱ የእቅድ አካባቢዎች ስር ያሉ የተለያዩ ነዋሪዎች እና የንግድ ተወካዮች እንዲሁም የከተማ ኮሚሽን አባላትን ያካተተ ቡድን ይሆናል። በአማካሪ ቡድኑ ውስጥ ክፍት የስራ ቦታ ከኖረ፣ ከተማው ለእነዚህ ባዶ ቦታዎች ህዝባዊ ሂደትን በመከተል (ኢ-ኒውስ) ማመልከቻ ለመቀበል ማስታወቂያ ያወጣል።

**4. ስለ ቦታው እና በዙሪያው ስላለው አካባቢ ብዝሃነት እና ታሪክ ተጨማሪ መረጃ ከየት አገኛለሁ?**

የፕሮጀክቱ ድህረገፅ alexandriava.gov/Landmark ስለገበያ ማእከሉ አሁን ያለውን እቅድና አከፋፈል፣ የቦታውን ታሪክ፣ እና የቦታውን ዲሞግራፊ በተመለከተ በዝርዝር የሚገልጽ ድህረ መረጃ ጥቅልን የያዘ ሊንክን ያቀርባል።

**5. ግንባታ እድሳት እንዲደረግ ለብዙ ዓመታት ጠብቀናል። በቦታው እድሳት እንዳይደረግ ያገደው ነገር ምንድን ነበር?**

ምንም እንኳን ከተማው ለዚህ ቦታ የግንባታ እቅዱን ቢያፀድቅም፣ የተለያዩ የገበያ፣ የባለቤት ትብብር፣ እና ገንዘብ ነክ ምክንያቶች የቦታውን የተለያዩ ባለቤቶች እና የግንባታ ድርጅቶች እቅዳቸውን እንዳይተገብሩ አግዷቸው ቆይቷል። ዛሬ ላይ ግን፣ የመኪና ማቆሚያውን ጨምሮ አጠቃላይ ሞሉ በተለያዩ ባለቤቶች ስር ያለ ሲሆን፣ አሁን ያሉት ባለቤቶች ለአጠቃላይ የገበያ ማእከሉ ቦታ ግንባታ እቅድ ለማስፈጸም ዝግጁ ናቸው።

**6. ይህን የእቅድ ሂደት ማድረግ ሳያስፈልጋቸው ለምን ወደግንባታ ቀጥታ አይገቡም?**

የ**2009** ላንድማርክ/ቫን ዶርን ኮሪደር እቅድ ለአካባቢው በማህበረሰቡ የታለመ ራእይ የሚሰጥ እና ለባለቤቶች፣ ለግንባታ ሰራተኞች እና ውሳኔ ሰጪዎች ስለወደፊት ግንባታ መመሪያ የሚሰጥ ዋና እቅድ/ማስተር ፕላን ነው። ስለሆነም፤ ሁሉም የግንባታ ማመልከቻዎች ፍቃድ እንዲያገኙ ማስተር ፕላኑን የሚያንፀባርቁ

# ላንድማርክ

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

መሆን አለባቸው። ከ**2009** ጀምሮ ከገበያ ለውጥ እና ከመጓጓዣ ጋር የተያያዙ የከተማ ፖሊሲዎች ምክንያት፣ አሁን ያሉት እቅዶች ባለንብረቱ ግንባታ ለማካሄድ ፈቃደ ለማግኘት ከማመልከቱ በፊት የተወሰነ ማሻሻያ ያስፈልጋቸዋል።

**7. አሁን ዳግም እቅድ ማውጣት እንዴት ዳግም ማሻሻያ/ግንባታ ማድረግን ያስከትላል?**

ባለፉት በርካታ ዓመታት ውስጥ፣ አሁን ያሉት የሞሉ ባለቤቶች በጋራ በመሆን ይህንን ሞል ሙሉ ለሙሉ ደግሞ ለመገንባት ብዙ ሕጋዊ እና ገንዘብ ነክ ችግሮችን አልፈዋል። ከዚህ በፊት የተሰጠው ፈቃድ የሞሉን መሀለኛውን ክፍል ለማሻሻል ብቻ ሲሆን በቢግ ቦክስ አንከር ችርቻሮ መቀጠል ላይ የተመሰረተ ነበር፤ ይህም አሁን የሚተገበር የችርቻሮ ሞዴል አይደለም። አሁን ግን በተጣመረ ባለቤትነት፣ አጠቃላይ ቦታው በጥልቅ እቅድ የሚያዝና ሙሉ ራእይ ይዞ ለወደፊት ተገልጋዮች አገልግሎት ይሰጣል።

በተጨማሪ፣ ይህ የዳግም እቅድ ሂደት የ2009 ላንድማርክ/ቫን ዶርን ኮሪደር እቅድ በቦታ አጠቃቀም የበለጠ ተለዋዋጭ እንዲሆን ለማስቻል ማሻሻያ የማድረግ እድልን የሚሰጥ ሲሆን፤ ይህም ወደፊት ዳግም እቅድ ማውጣት ሳያስፈልግ ፈጣን የገበያ ምላሽ እንዲኖር ያስችላል።

**8. በእቅድ ሂደቱ ላይ ትምህርት ቤቶች ግምት ውስጥ ይገባሉ**?

አዎ። የ2009 ላንድማርክ/ቫን ዶርን ኮሪደር እቅድ ላንድማርክ ሞል አካባቢን ጨምሮ በላንድማርክ/ቫን ዶርን ኮሪደር እቅድ አካባቢ የማህበረሰብ መገልገያዎችን (ማለትም ትምህርት ቤት፣ የማህበረሰብ/የመዝናኛ ማእከላት፣ የእሳት አደጋ/ፖሊስ ጣቢያዎች፣ እና ሌሎች የከተማ ተቋማት) እንዲኖሩ ይመክራል።

**9. ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶች እንዴት ታሳቢ እየተደረጉ ነው፣ እንዲሁም ተመጣጣኝ የባለቤትነት አማራጮች ይኖራሉ?**

ቀጥሎ የቀረቡትን የመሳሰሉ ያሉትን መሳሪያዎች በመጠቀም በዚህ የእቅድ ሂደት ላይ ተመጣጣኝ የቤት እቅድ አማራጮች ይቀርባሉ፥

i. ክፍል 7-700 ዞኒንግ ድንጋጌ በመጠቀም ቦነስ ዴንሲቲና ቁመት፣

ii. ለቤት ግምባታ ትረስት ፈንድ ፈቃደኛ የግምባታ ተቋራጮች አስተዋጽኦ፣

iii. ለትርፍ ካልተቋቋሙ ግንባታ ተቋራጮችና የቤቶች/አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር መተባበር፣

iv. ከከተማ ተቋማት ጋር ማገናኘት፣

v. ብድሮችና ሌሎች የገንዘብ ድጋፍ መርሀግብሮች።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን alexandriava.gov/Housing የሚለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ።

**10. ከተማው ለዌስት ኢንድ ትራንዚትዌይ መንገድ ፍቃድ ማግኘት ወይም አለማግኘታችንን የሚያውቀው መቼ ነው?**

ከተማው የግንባታ ፍቃድ ማግኘት ወይም አለማግኘቱን የሚያውቀው በጃንዋሪ 2019 ሲሆን የስማርትስኬል ብድር/ፍቃድ ማግኘቱን የሚያውቀው ደግሞ በፀደይ/በበጋ 2019 መጀመርያ ላይ ይሆናል። ስለ ዌስት ኢንድ ትራንዚትዌይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎትን alexandriava.gov/WestEndTransitway የሚለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ።

**11. የ2009 ላንድማርክ ቫን ዶርም ኮሪደር እቅድ የመጓጓዣ ማውረጃ/መጫኛ ቦታውን (ትራንዚት ሃብ) በላንድማርክ ውጭኛው ክፍል በኩል ሳይሆን መሀለኛው ክፍል ላይ ለመገንባት ለምን ፈለገ?**

ለወደፊት የታቀደው ሞል የክልሉን እና አጎራባች ሰፈራዎችን ፍላጎቶች የሚያሟላ እና ከአጎራባች አካባቢዎች ጋር ለማገናኘት የሚያስችል ለተለያየ አገልግሎቶች የሚውል፣ ልዩ የሆነ ስነ ህንጻ፣ ትራንዚት፣ የማህበረሰብ ቦታዎች ያሉት የከተማ መንደር ለመፍጠር የሚያስችል ነው ተብሎ ይታሰባል። ቀጣዩ የመጓጓዣ ማውረጃ/መጫኛ ቦታው በቀጣይ ከሚሰሩት ምግብ ቤቶች፣ ሱቆች፣ የስራ ቦታዎች እና መኖርያ ቤቶች እንዲመች ሆኖ መሃል ላይ የሚሰራ ይሆናል። የመጓጓዣ ማውረጃ/መጫኛ በውጭኛው በኩል ማድረግ ማለት የዱክ ጎዳና መስፋት ይኖርበታል ማለት ነው፣ ይህም የ2009 እቅድ ግብ ወይ የአሁን አጠቃላይ የመንገድ መመርያ አይደለም።

**12. አሁን ያለው የመጓጓዣ ማውረጃ/መጫኛ በጊዜያዊነት ወደ ሌላ ቦታ ሊቀየር ይችላል**?

በአሁኑ ወቅት የአውቶቡስ ማውረጃ/መጫኛውን በጊዜያዊነት ወደ ሌላ ቦታ ለማዘዋወር ምንም አይነት እቅድ የለም። ምንም እንኳ ሞል ውስጥ ያሉት ሱቆች ስራ እየሰሩ ባይሆንም፣ ሞሉ ጥበቃ የሚደረግለትና ለጊዜውም ለካርፔንተርስ ሼልተር እና ሌሎች ጊዜያዊ አገልግሎቶች ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ይገኛል።

**13. ከተማው አሁን ሞሉ በሚገኝበት አካባቢ ላለው የእግረኛ መንገድ ደህንነት ለምን ጊዜያዊ ማሻሻያ አያደርግም**?

በዋከር ጎዳና እና በዱክ ጎዳና ላይ ያሉትን ጨምሮ፣ የእግረኛ ማቋረጫ የመብራት ምልክቶች እና በዱክ በሰሜን እና ደቡብ አቅጣጫ ከዋከር ጎዳና በ 395 ላይ አዲስ የእግረኛ መንገድ ግንባታን ጨምሮ የእግረኛ መንገድ ማሻሻያ ግንባታዎች በቅርብ ዓመታት ውስጥ ተደርጓል። የስማርትስኬል ግራንት (በቅርቡ ይሰጣል ተብሎ የሚጠበቀው) ወደ ላንድማርክ ሞል አካባቢ ለሚኖረው የወደፊቱ የእግረኛ መንገድ ማሻሻያ ግንባታ ይውላል።